4ኛ ዓመት ቁጥር 11
4th Year No. 11

ሐረር የካቲት 25 ቀን 1991
Harar March 4/1998

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE



| | | |
|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ 0.50 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |



ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 17/1991
የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ለማሻሻል የወጣ
አዋጅ ቁጥር 17/1991 ---------------------------------------------------ገጽ 115
ማረሚያ ቁጥር 1/1991 ---------------------------------------------------ገጽ 116

## አዋጅ ቁጥር 17/1991

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ።

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### 1. አጭር ርዕስ ፤

ይህ አዋጅ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 17/1991 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 1. ማሻሻያ ፤

የክልሉ ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. በአንቀጽ 7 ሥር የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 7 እና 8 ተጨምሯል።

«7. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ማናቸውም የፍትሐ ብሔር ክሶችና ከ10 ዓመት በታች በሆነ እሥራት /ጽኑ እስራት/ የሚያስቀጡና በክልሉ የዳኝነት ሥልጣን ሥር የሚወድቁ የወንጀል ክሶች በአንድ ዳኛ በሚመራ ችሎት ሊታዩ ይችላሉ።»

«8. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 7 ሥር የተደነገገው የችሎት አሰራር ተግባራዊ የሚሆንበት ጊዜና ሁኔታ የሚወሰነው የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ይሆናል።»

ስለሆነም የዚህ ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ በፌደራሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 80/4/ ድንጋጌ በተሰጠው ውክልና መሠረት የሚቀርቡትን የወንጀል ጉዳዮችና በይግባኝ የሚቀርቡ ማናቸውንም ጉዳዮች አያጠቃልልም።

2. አንቀጽ 12 ሥር የሚከተለው ንዑስ አንቀጽ 16 ተጨምሯል።
«16. ሶስት ዳኞች በሚሰየሙበት በየትኛውም የክልሉ ፍርድ ቤት ችሎት በማንኛውም ምክንያት ችሎት ሲጓደል ቀጥሎት ከሚገኘው የበታች ፍርድ ቤት ዳኞች አንዱን ችሎት እንዲያሟላ ለማዘዝ ይችላል።

3. አንቀጽ 32 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል።

«2. የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት በአንድ ሰብሳቢና በሁለት ዳኞች የሚያስችል ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ችሎት በአንድ ዳኛ ያስችላል።»

3. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ ፤

ይህ ማሻሻያ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር የካቲት 25 ቀን 1991

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት ፕሬዝዳንት

---

ማረሚያ ቁጥር 1/1991 ዓ.ም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፍርድ ቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 8/1991 ነጋሪ ጋዜጣ 3ኛ ዓመት ቁጥር 2 አንቀጽ 3 ሥር የተደነገጉት አንቀጽ 4 ተብሎ እንዲነበብ ሆኖ አንቀጽ 4 ሥር የተደነገገው አንቀጽ 3 ተብሎ ታርሟል።